# የንጥር-ጥናት አውትላይኖች
# ኤርሚያስ እና ሰቆቃወ ኤርሚያስ

## ቁልፍ መግለጫዎች

ያሕዌ ርኅሩኅ አምላክ ነው፣ ርኅሩኅ በመሆኑም
ኤርምያስ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበር፤
ስለዚህ፣ እንዲገልጠው፣ ለእርሱ እንዲናገር እና እንዲወክለው እግዚአብሔር
ድል-ነሺ የሆነውን ነቢዩ ኤርሚያስን በለቅሶውም እንኳን ሳይቀር መጠቀም ችሏል።

የእስራኤልን ኃጢአት እና የእግዚአብሔርን ቁጣ፣ ተግሳጽ እና ቅጣት
በሚመለከት ንግግር የተሞላው የኤርሚያስ መጽሐፍ፣
እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ያለው ውጥኑ ለመገለጡ የሆነች የእግዚአብሔር ሙላት ትሆን ዘንድ
ቤተ ክርስቲያንን፣ የእግዚአብሔርን አምሳያ፣ እንደ የእግዚአብሔር መጨመር፣ እንደ የእግዚአብሔር መተለቅ
ለማፍራት በሆነ ግብ ለእርካታቸው እና ለድሰታቸው ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ለማደል
የሕያው ውኃዎች መፍለቂያ፣ ምንጭ መሆኑን ይገልጣል።

እግዚአብሔር በከባቢ ሁኔታ እና በክስተቶች የማይለወጥ
ዘላለማዊ እና ሊለወጥ የማይችል ነው፣
የእግዚአብሔር ዙፋን የዘላለማዊው እና የማይለወጠው አገዛዙ ዙፋን ነው፤
ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ማንነት እና ዙፋን በሚመለከተው ንግግሩ፣
ኤርሚያስ ከሰብአዊ ስሜቱ ወጣ፣ የእግዚአብሔር ማንነት እና ዙፋን ነካ፣
ወደ የእግዚአብሔር መለኮትነት ውስጥም ገባ።

እግዚአብሔር እንደ ሸክላ ሠሪያችን በቀደመ ውሣኔው መሠረት
እርሱን ራሱን ለመያዝ ማድጋዎቹ፣ መያዣ ዕቃዎቹ እንድንሆን በሉዓላዊነቱ ፈጠረን፤
እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበት ዓላማ፣
ለመገለጡ እንዲሆን የእግዚአብሔር ታላቅ፣ ብዙዎች የተካተቱበት ማድጋ፣
ለክርስቶስ አካል መገንባት እንደ ሕይወት ክርስቶስን ለመያዝ እና በክርስቶስ ለመሞላት፣
ሰውን ከሸክላ የተሠራ የእርሱ መያዣ ለማድረግ ነበር።

በእግዚአብሔር ልብ መሠረት እንደሆነው እረኛ፣ የበጎች ታላቅ እረኛ የሆነው ክርስቶስ
የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት ለመንከባከብ
ሐዋርያዊውን አገልግሎት ከሰማያዊው አገልግሎቱ ጋር በማካተት እረኝነቱን እየቀጠለ ነው፤
በጌታ ምለሳ ዛሬ፣ የክርስቶስን አካል የሚገነባው የእረኝነት እንክብካቤ
የእርስ በርስ የእረኝነት እንክብካቤ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል፣
እንዲሁም ለመንጋው ሁሉን-ያካተተ፣ በርኅራኄ የተሞላ እንክብካቤ በማድረግ
አንዳችን ሌላችንን በእግዚአብሔር መሠረት መንከባከብ ያስፈልገናል።

ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን፣ ክርስቶስ እንደ ዳዊት ቁጥቋጥ
ቤዛነታችን እና ጽድቃችን እንዲሆንልን ያስፈልጋል፤
ይህ ኢኮኖሚውን ለማከናወን ወደ ማንነታችን ውስጥ ራሱን ያድል ዘንድ
ሕይወታችን፣ የውስጥ የሕይወት ሕጋችን፣ አቅማችን እና ሁሉ ነገራችን እንዲሆን
ሦስታንዱን አምላክ ወደ ውስጣችን ያመጣዋል፤
ይህ እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ እንሆን ዘንድ
እግዚአብሔርን ማወቅ፣ እግዚአብሔርን መኖር እና ተመላኪነቱን ሳይጨምር
በሕይወት እና በባህርይ እግዚአብሔርን መሆን የምንችልበት አዲሱ ኪዳን ነው።

*© 2020 Living Stream Ministry*

መልእክት አንድ

## ኤርምያስ፣ የርኅሩኅ አምላክ ርኅሩኅ ነቢይ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 1፡1፣ 4-8፣ 10፣ 18-19፤ 4፡19፤ 9፡1፣ 10፤ 13፡17

**I. ኤርምያስ በትውልዱ ካህን ነበር፣ ነገር ግን ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብ ሁሉ ጭምር ነቢይ እንዲሆን በእግዚአብሔር ተጠራ፤ ስለዚህ እርሱ ካህን-ነቢይ ነበር—ኤር. 1፡1፣ 4-8።**

**II. ይነቅል እና ያፈርስ ዘንድ፣ ያጠፋና እና ይገለብጥ ዘንድ፣ ይገነባ እና ይተክል ዘንድ ያሕዌ ኤርምያስን በአሕዛብ ላይ እና በመንግሥታት ላይ ሾመው—ቁ. 10፦**

ሀ. መንቀሉ፣ ማፍረሱ እና ማጥፋቱ የያሕዌ መገልበጥ ሲሆኑ፣ መገንባቱ እና መትከሉ ደግሞ የያሕዌ ከፍ ከፍ ማድረግ ናቸው።

ለ. ይህ ኤርምያስ ከሚለው ስም ከሁለት ትርጉሞች ጋር ይዛመዳል፦ "ያሕዌ ከፍ ከፍ ያደርጋል" እና "ያሕዌ ይገለብጣል።"

**III. ያሕዌ ኤርምያስን በምድሪቱ ሁሉ ላይ፣ በይሁዳም ነገሥታት፣ በአለቆችዋ፣ በካህናትዋ እና በምድሪቱ ሕዝብ ላይ እንደ ተመሸገ ከተማ፣ እንደ ብረት ዓምድ እና እንደ ናስ ቅጥር እንዲሆን አደረገው፤ ይዋጉታል ነገር ግን አያሸንፉትም—ቁ. 18-19፦**

ሀ. በምድር ላይ ሁልጊዜም በእግዚአብሔር እና እርሱን በሚቃወሙ እንዲሁም ከእርሱ ጋር በሚዋጉ መካከል ውጊያ እየተፋፋመ ነው—ኤፌ. 6፡12።

ለ. እግዚአብሔር ቀጥታ በራሱ ሳይሆን ነገር ግን በእርሱ በተላኩ በአገልጋዮቹ በኩል ይዋጋል—1 ጢሞ. 1፡18፤ 6፡12፤ 2ጢሞ. 4፡7።

ሐ. እግዚአብሔር የተቃወሙትን ለመዋጋት ሠራዊቱን—ኤርሚያስ የሚባልን ወጣት ሰው—ላከ፦

1. ኤርምያስ የተመሸገ ከተማ፣ የብረት ዓምድ እና የናስ ቅጥር እስከሚሆን ድረስ በእግዚአብሔር የታጠቀ ነበር—ኤር. 1፡18።
2. የያሕዌ አንድ-ሰው ሠራዊት ከሆነው ከኤርሚያስ ጋር የተዋጉ በእውነት እየተዋጉ የነበሩት ከያሕዌ ጋር ነው—ቁ. 19።
3. ያሕዌ ከእርሱ ጋር ስለነበረ ማንም ሊያሸንፈው አልቻለም—ቁ. 19።

**IV. ኤርምያስ ለእግዚአብሔር የሚናገር ድል-ነሺ ነበር—ቁ. 9-10፤ 2፡1-2፦**

ሀ. በምሳሌ ዘመን፣ ድል-ነሺዎቹ ነቢያቱ ነበሩ፤ ሁሉም እውነተኛዎቹ ነቢያት ድል-ነሺዎች ነበሩ።

ለ. አብዛኛው የእግዚአብሔር ሕዝብ ተበታትኖ ሳለ፤ በእግዚአብሔር የጸናውን ምስክርነት ጠብቆ ለማቆየት አንዳንዶች የእግዚአብሔር ድል-ነሺዎች ለመሆን መነሣታቸው አስፈላጊ ነበር።

ሐ. ነቢያቱ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ንግግር ተናገሩ፣ በዚህም ንግግር መሠረት በንጉሥ ዳዊት እና በነቢዩ ናታን እንደታየው በተወሰነ መልኩ የእግዚአብሔርን ስልጣን አንቀሳቀሱ—2 ሳሙ. 7፡1-17፤ 12፡1-15።

መ. በራእይ 2 እና 3 ያሉት ድል-ነሺዎች የነቢያቱ ምሳሌ መፈጸም ናቸው።

ሠ. እንደ ድል-ነሺ፣ ኤርምያስ ተጻራሪ-ምስክር ነበር፦

1. የእስራኤል ልጆች ተበታተኑ፣ ኤርምያስም ተጻራሪ-ምስክር ለመሆን በእግዚአብሔር ተጠራ—ኤር. 27፡1-15።
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት በኃጢአት ዘቅጠው እንደነበረ እና ወደ ባቢሎን እንዲማረኩ በማድረግ እነርሱን ለመቅጣት ባቢሎንን ለመጠቀም እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደወሰነ አልገባቸውም ነበር—15፡12-14።
3. እስራኤል እንዲህ ወዳለው ግራ ወደተጋባ ሁኔታ ውስጥ በመውደቃቸው ምክንያት፣ በያሕዌ የተሰጠውን ቃል በመናገር እና ከሐሰተኛ ነቢያት ተቃራኒ በመሆን፣ ድል-ነሺው ኤርምያስ፣ ተጻራሪ-ምስክር ነበር—27፡16—28፡17።

**V. እንደ ልዩ መገለጫው እና አቋሙ የኤርምያስ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ከእግዚአብሔር ጽድቅ ጋር ደምሮ ይዟል—9፡10-11፤ 23፡5-6፤ 33፡16፦**

ሀ. አምላካችን በርኅራኄ እና በሐዘኔታ የተሞላ ርኅሩኅ አምላክ ነው፤ ሆኖም ግን እርሱ ፍጹም ጻድቅ ነው—9፡10-11፤ 23፡6።

ለ. በኤርሚያስ መጽሐፍ መሠረት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በደግነት የሆነ እንክብካቤውን፣ ርኅራኄውን እና ሐዘኔታውን ያካተተ ነው፤ ምርጥ ሕዝቡን እስራኤልን ሲቀጣ ሳለ እንኳ ለእነርሱ ርኅሩኅ ነው—ሰቆ. ኤር. 3፡22-23።

ሐ. በኤርምያስ 9፡10-11 እና 17-19 ያሉት ቃላት እርሱ እስራኤልን በማስተካከሉ እነርሱ ላይ የመጣውን መከራ በተመለከተ የያሕዌን ስሜት ይገልጣሉ፡-

1. ምንም እንኳን ያሕዌ እስራኤልን እየቀጣ የነበረ ቢሆንም ለእነርሱ አዛኝ ነበር።
2. በቁጥር 18 ያሉት ሐኛ እና [የእኛ] የሚሉት ቃላት ያሕዌ በመከራ ከነበሩት ሕዝብ ጋር ራሱን እንዳያያዘ እና በመከራቸው ከእነርሱ ጋር አንድ እንደነበር ያመለክታሉ።
3. ያሕዌ ራሱ ከሕዝቡ ጋር በሐዘኔታ ሲያለቅስ ነበር።

## VI. የኤርምያስ መጽሐፍ ኤርምያስ ርኅሩኅ ልቡን በመግለጥ፣ ስለ ሁኔታው፣ ስለ ማንነቱ እና ስለ ስሜቶቹ ለእኛ የሚነግርበት ግለ-ታሪኩም ጭምር ነው፡-

ሀ. እግዚአብሔር ርኅሩኅ፣ አፍቃሪ፣ አዛኝ እና ጻድቅ ነው፣ ለእርሱ ለመናገር እርሱን ለመግለጥ የእርሱ አፍ ለመሆን ዓይን-አፋሩ ወጣት ሰው ኤርምያስ በእግዚአብሔር ተነካ—3፡6-11፤ 4፡3-31፤ 32፡26-27፤ 33፡1-2።

ለ. ያሕዌ ርኅሩኅ አምላክ ነው፣ ርኅሩኅ በመሆኑም ኤርምያስ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበር፤ ስለዚህ፣ እንዲገልጠው፣ ለእርሱ እንዲናገር እና እንዲወክለው እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስን መጠቀም ችሏል—2፡1-3፡5፤ 4፤19፤ 9፡1፣10።

ሐ. ያሕዌ ግብዝ አምላኪዎቹን ለማረም መጣ፣ ኤርምያስም ለያሕዌ ማረም ምላሽ ሰጠ፤ የነቢዩ ምላሽ እጅግ ለስላሳ፣ አዛኝ እና ርኅሩኅ ነበረ—8፡18-19፣ 21-22፤ 9፡1-2፤ 10፡19-25።

መ. ኤርምያስ በእግዚአብሔር ምትክ አለቀሰ፤ ለቅሶው የእግዚአብሔርን ለቅሶ ገለጠ—4፡19፤ 9፡1፤ 13፡17፦

1. በለቅሶው ኤርምያስ እግዚአብሔርን ወከለ—9፡10።
2. በማልቀሱ ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስለነበር፣ በኤርምያስ ለቅሶ ውስጥ እግዚአብሔር አለቀሰ ማለት እንችላለን—13፡17።

ሠ. ኤርምያስ አብዛኛውን ጊዜ ስለሚያለቅስ፣ ዋይ ዋይ ስለሚል እንኳን ሳይቀር የሚያለቅሰው ነቢይ ተብሏል—ሰቆ. 1፡16፤ 2፡11፤ 3፡48፡-

1. ምንም እንኳን እግዚአብሔር በሕዝቡ ምክንያት ቢያዝን እና ቢጎዳም፣ በምድር ላይ እነዚህ ስሜቶች የነበሩትን ሰው ማግኘት ነበረበት።
2. መንፈሱ በዚያ ልዩ በሆነው፣ በኤርምያስ ላይ በመጣ እና ስሜቶቹን በኤርምያስ መንፈስ ውስጥ ባኖረ ጊዜ፣ ያኔ ነቢዩ በሐዘን የተሞላውን የእግዚአብሔርን ስሜት መግለጥ ችሏል።
3. የኤርምያስን መጽሐፍ ስናነብ፣ ቢያለቅስም እንኳን፣ ስሜቱ የተገራ እንደሆነ ግንዛቤው ይኖረናል—4፡19፤ 9፡1፣ 10፤ 13፡17።
4. እግዚአብሔር ወደ እርሱ ይመጣ ዘንድ እና በልቡ ውስጥ የነበሩትን በሐዘን የተሞሉ ስሜቶች ለመግለጥ ይጠቀምበት ዘንድ በሐዘን የተሞላው እና የሚያነባው የኤርምያስ ስሜት ተገርቶ እና ተገድቦ ነበር።

## VII. እግዚአብሔር በእኛ በኩል በሙላት እንዲገለጥ፣ መንፈሳዊ ስሜቶች ያሉን፣ አንዳችን ለሌላችን የምንራራ እና እግዚአብሔርን በእንባ ማገልገል የምንችል ልንሆን ያስፈልጋል—ያዕ. 5፡11፤ ዘጸ. 34፡6፤ መዝ. 103፡8፦

ሀ. መንፈሳዊ ሰው በስሜቶች የተሞላ ነው፤ አብልጠን መንፈሳዊያን ስንሆን፣ ስሜቶቻችን አብልጠው ይበለጥጋሉ—1 ቆሮ. 4፡21፤ 2 ቆሮ. 6፡11፤ 7፡3፤ 10፡1፤ 12፡15፡-

1. ስሜቶቻችን ደስ የሚያሰኙ እና ርኅሩኅ እስኪሆኑ ድረስ ጌታ በእኛ ላይ እንዲሠራ ያስፈልገናል።
2. እግዚአብሔር በእኛ ላይ በሠራ፣ በቀጣን እና ባስተካከለን ጊዜ ሁሉ፣ ስሜቶቻችን አብልጠው ደስ የሚያሰኙ እና የሌሎችን ስሜት በቀላሉ የሚረዱ ይሆናሉ፤ ይህ የውጪው ሰው በመሰበሩ የሚገኝ ጥልቁ ትምህርት ነው—4፡16።

ለ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን ርኅሩኅ ልንሆን ያስፈልገናል—ኤፌ 4፡32፦

1. አብረውን ያሉ አማኞችን ላይ መፍረድ እና መኮነን የለብንም ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳለን እንዲሁ እነርሱን ይቅር በማለት ለእነርሱ ደግ እና ርኅሩኅ መሆን አለብን—ሉቃ. 6፡37፤ ኤፌ. 4፡32።
2. ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን አብዝተን ስንለማመደው፣ ልባችን አብዝቶ ርኅሩኅ ይሆናል፣ ርኅሩኅ ስንሆን ደግሞ፣ ሌሎችን ይቅር እንላለን።

ሐ. ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን በእንባ አገለገለ እንዲሁም ቅዱሳንን በእንባ ገሠጸ—ሐዋ. 20፡19፣ 31፤ ፊልጵ. 3፡18፡-

1. እንዴት እንደሚለቀስ ወይም እንባ እንደሚፈስስ ካላወቅን፣ በጣም መንፈሳውያን አይደለንም።
2. ነፍሳችንን እንደ ጠቃሚ አካል በመጠቀም በመንፈሳችን ስንኖር፣ በእንባ ጌታን ለማገልገል እና ቅዱሳንን ለመገሥጽ የምንችል እንሆናለን—ሐዋ. 20፥19፣ 31።

መ. ጳውሎስ "በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት" ጋር ለቆሮንቶስ ሰዎች "በብዙ እንባ" ጻፈላቸው—2 ቆሮ. 2፥4፦

1. የጳውሎስ አገላለጽ ርኅሩኅ እና በሚያገለግል ሕይወት የቅርብ በሆነ ግድ መሰኘት የተሞላ ነበር—11፥28፤ 12፥15።
2. በ2ኛ ቆሮንቶስ 7 ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያለውን ጥልቅ፣ ርኅሩኅ እና የቅርብ የሆነ ግድ መሰኘት አስተላልፏል፤ የእርሱ ቃል በጣም የሚነካ ነበር—ቁ. 2-3።
3. የጳውሎስ አገላለፅ ርኅሩኅ እና የቅርብ በሆነ ግድ መሰኘት የተሞላ ስለነበር፣ ኃይል እና ተጽዕኖ ነበረው፣ አማኞችንም በጥልቀት ለመንካት ችሏል።

ሠ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በለቅሶ ሸለቆ ውስጥ ስናልፍ፣ እግዚአብሔር ይህን ሸለቆ ምንጭ ያደርገዋል፤ ይህ ምንጭ መንፈስ ነው—መዝ. 84፥6፤ ዮሐ. 4፥14፤ 7፥38-39፦

1. ወደ ጽዮን በሚወስዱት ጎዳናዎች ላይ አብዝተን ስናለቅስ (መዝ. 84፥5)፣ አብዝተን መንፈስን እንቀበላለን፤ እያለቀስን ሳለ፣ በመንፈስ እየተሞላን ነው፣ መንፈስም ምንጫችን ይሆናል።
2. የምናፈስሰው እንባ የእኛ ነው፣ ነገር ግን እነዚህ እንባዎች የኋለኛው ዝናብ፣ በረከት የሆነውን መንፈስ የሚሆንን ምንጭ ያመጣሉ—ዘካ. 10፥1፤ ገላ. 3፥14፤ ኤፌ. 1፥33።

© 2020 Living Stream Ministry